የባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘናና ምዝገባ ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

መግቢያ

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ በተለይም በምህንድስናና በጤና ሙያ የአገልግሎት ጥራትና የሥነ ምግባር ደረጃ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ወድቆ ይገኛል። ባለሙያው ትኩረቱን በገቢ መጠን ላይ ብቻ በማተኮር ፍትኃዊ ሥነ ምግባር የተላበሰ አገልግሎት ማግኘት ብርቅ እየሆነ መምጣቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ለዚህም ማስረጃ በመገናኛ ብዙሃን በየጊዜው የሚሰሙት የሙያ ግድፈቶችና በዚህም ሳቢያ የሚጠፋው የሰዎች ሕይወት ነው።

ወደ መሬት የሚሰርጉ ሕንፃዎች የረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲጠበቅባቸው በዲዛይን ለውጥ ወይም በሌላ በአጭር ጊዜ የሚፈርሱ ወይም የሚበላሹ ግንባታዎች፤ ደረጃውን ባልጠበቀ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የሚከሰቱ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ሁሉ በአብዛኛው ከባለሙያ ጥንቃቄ ጉድለት እንደሚሆኑ ግልፅ ነው።

በተመሣሣይ በሕግ ባለሙያዎች የስነ ምግባር ችግር ፍትህ የሚዛባበት፤ ከባላንጣ ጋር በጥቅም መገናኘት፤ ከሁለት ወገን ጥቅም የማግኘት አካሄድ፤ ባለጉዳይ በሕጉ መሠረት ሊፈረድለት እንደማይችል እያወቁ ዜጎች ያለአግባብ በፍርድ ቤት እንዲጉላላና በገቢ ማዳበሪያነት ብቻ መሥራት የመሣሠሉት ችግሮች ይታያሉ።

የሥነ ምግባርና የሙያ ግድፈት በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ቢታይም ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ዘርፎች በተለይም በምህንድስናና በጤና ዘርፎች ላይ ብቻ ነው። ሆኖም የጥናቱ እንኳር ውጤት ለማንኛቸውም የሙያ ዘርፎች ማገልገል ስለሚችል ወደፊት ተቋሙ ሁሉን ዓቀፍ የሙያ ብቃት ምዘናና የባለሙያ ምዝገባ ሥርዓት ማስፈን እንደሚችል ይታመናል።

በምህንድስናና ዘርፎች በተለያዩ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት መኖሩ አይካድም። ሆኖም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ የመጡትን የሙያ ግድፈቶች መቆጣጠር አልቻሉም።

ለዚህም ሶስት መሠረታዊ ምክንያቶች፤

1) ትክክለኛው የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት በአንድ የመንግሥት ተቋም ብቻ የሚሰጥ ባለመሆኑና ይልቁንም የሙያ ማህበራትን እገዛ የሚያካትት በመሆኑ፤

2) አሁን ባሉት አገልግሎቶች ውስጥ ለባለሙያዎች የተሟላ የሙያ ብቃት ምዘናና ተከታታይ የሙያ ማበልፀጊያና የሥነ ምግባር መከታተያ ሥርዓት የተካተተ ባለመሆኑ፤

3) በሥራ ላይ ያሉት የባለሙያ ምዝገባ አካላት አገልግሎቱን ለመስጠት ከተቋቋሙበት የሕግ ማዕቀፍ በተጨማሪ በሚመለከተው አገር አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ አካል ዕውቅና (accreditation) ያልተሰጣቸው በመሆኑ ነው።

በሌላ በኩል ለተመሣሣይ ምህንድስና ሙያ በተለያዩ የብቃት ምዘና ተቋማት የተቀመጡ መስፈርቶች በእጅጉ መለያየት፤ የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት በአብዛኛው የተመሠረተው አመልካቾች በሚያስገቡት የትምህርትና የሥራ ልምድ ሰነድ ላይ ብቻ መሆኑና፤ ይልቁንም የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በበቂ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ፤ በየመሥሪያ ቤቶቹ የተዘረጉት ሥርዓቶች ውጤታማ ናቸው ለማለት ያዳግታል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፤ የዚህ ጥናት መነሻ በተለይ የምህንድስናና የሕክምና ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ሲሆን ይህንኑ አስመልክቶ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተካሄዱ ሁለት የምክክር መድረኮች የችግሩን ግዝፈት ለመረዳትና እንደ አገር መፍትሔ ሊገኝ በሚችልበት አግባብ ላይ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎችና የዘርፍ መሥሪያ ቤት ተወካዮች ጋር በቂ ውይይት ተደርጎበታል።

የጥናቱ ዓላማ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የሙያ ብቃት ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አንድ ወጥ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ፅ/ቤት ዕውቅና በተሰጠው የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና ተቋም ማቋቋም ነው። ይህ በአዲስ መልክ የሚቋቋም ተቋም በቴክኖሎጂ እየታገዘ በዘመናዊ መልክ ከሙያ ማህበራትና ከዘርፍ ተቋማት ጋር የሚሠራ ተቋም እንዲሆን ይጠበቃል።

1. <u>የአዋጁ አስፈላጊነት</u>

በመሠረቱ የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት በሙያ ሥነ ምግባር ኮድና በተከታታይ የባለሙያ ስልጠና የሚታገዝና ለሙያ እድገት የማህበረሰቡን ደህንነትና ጤንነት ማዕከል ያደረገ የሙያ አገልግሎት ነው።

ይህ ጥናት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፤ የምዝገባው አገልግሎት ከሞላ ጎደል እየተሰጠ ቢሆንም የባለሙያ ዐቅም ግንባታና የሙያ ልማት የተጠናከረ ባለመሆኑና በዚህም ምክንያ በሙያውና በባለሙያዎች ብቃት ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ የሙያ ግድፈቶች እየጨመሩ በመምጣታቸው፤ የችግሩ ምንነት በመረዳት ወቅታዊና ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት ነው።

ለችግሩ መፍትሔ ካልተሰጠው መንግሥት ሊያከናውናቸው ያሰባቸውና በተከታታይ የተቀረፁ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ውስጥ የተካተቱ ታላላቅ ፕሮጀክቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ የማህበረ ሰቡ ደህንነትና ጤንነት አደጋ ላይ ስለሚጥል በጥናት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የባለሙያዎች ብቃት ምዘናና ምዝገባ ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ነው።

2. የሃገራችን ልምድ

የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ለግለሰብና ድርጅታዊ ተከታታይነት ላለው የሙያ እድገት አስተዋፅዖ የሚያደርግ ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ የሚጠቅመውም ባለሙያዎች ሁልጊዜ ሙያቸውን እንዲያሳድጉ ብሎም ጥራት ያለው ሙያዊ አገልግሎት እንዲሰጡ በዚህም ሥራቸው የማህበረ ሰቡን ደህንነትና ጤንነት ጥያቄ ውስጥ የማያስገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ነው።

በዚህ ሥርዓት ውስጥ አንድ ባለሙያ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሲመረቅ፤ በጀማሪ ባለሙያነት ይመዘገባል። የተወሰኑ ዓመታት በሙያው ልምድ ሲያገኝና ሙያውንም ለማሳደግ መደበኛ ጥረት ማድረጉ ሲረጋገጥ፤ ደረጃውን አሻሽሎ በድጋሚ ይመዘገባል። ይህ የማሻሻያ ምዝገባ የመጨረሻውን ደረጃ እስኪያገኝ ድረስ ለተከታታይ ጊዜያት ይከናወናል።

የዚህ ሥርዓት አተገባበር ላይ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የተለያዩ ልምዶች እንዳሉ በርካታ የመረጃ ምንጮች ያሳያሉ። ለዚህ ጥናት መነሻ እንዲሆን በአገር ውስጥና በተመረጡ በውጭ አገራት ውስጥ ያሉትን ልምዶች እንደሚከተለው ተጠናቅረዋል።

2.1 በምህንድስና ዘርፍ

በአገራችን የባለሙያ ምዘገባና ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት አዲስ አይደለም። በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ለተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሥርዓቱ ሲተገበር ቆይቷል። በዚህ ረገድ በዋነኛነት የሚጠቀሰው የኮንስትራክሽን ዘርፍ የነበረውና አሁንም ያለው የምዝገባ ሥርዓት ነው።

በወቅቱ፤ በተለያየ ጊዜ የሕንፃና ትራንስፖርት ኮንስትራክሽንና ዲዛይን ባለሥልጣን፤ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር፤ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር፤ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች በተለይም ለሲቪል መሐንዲሶች፤ ለሕንፃ መሐንዲሶች፤ ለአርኪቴክቶች፤ በተወሰነ ደረጃም ተዛማጅነት ላላቸው የኤሌክትሪክና ሜካኒካል መሐንዲሶች፤ የባለሙያ ምዘገባና ብቃት ማረጋገጥ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይተዋል።

ከኮንስትራክሽን ዘርፍ ውጭ፤ በምህንድስና ዘርፍ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ (አሁን የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን)፤ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መገናኛ ሚኒስቴር፤ የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ (አሁን የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲትዩት)፤ በተለያየ ደረጃ አገልግሎቱን ሲሰጡ ቆይተዋል።

የተዘረዘሩት የአገር ውስጥ መሥሪያ ቤቶች ይሰጡት ስለነበራቸውና አሁን ስላላቸው አገልግሎት ዝርዝር መረጃ ከየመሥሪያ ቤቶቹ ሰነዶች ማግኘት ይቻላል።

በአገር ውስጥ ያለው ልምዶች ዋና ዋና መገለጫቸው፣

1) የሙያ ብቃት ማረጋገጫው በአመልካቾች ሰነድ ምርመራ ላይ ብቻ የተመሠረቱ መሆናቸው፤

2) ባለሙያዎች ሙያቸውን በተከታታይ ሊያዳብሩ የሚችሉበት ዕድል የሌለ መሆኑ፤

3) በሙያ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ ሥራ ላይ የሙያ ማህበራት ሚና በጣም ውሱን መሆኑ፤

4) በተለያዩ የባለሙያነት ደረጃ ልክ የሙያ ብቃት ልዩነት መኖሩን የማያረጋግጡ መሆናቸው፤

5) በሙያዊ አገልግሎቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን የሚከታተሉ የሚቆጣጠሩ ያለመሆናቸው፤

6) የሙያ ብቃት አረጋጋጭ አካላት ከማቋቋሚያ አዋጅ ውጭ አገልግሎቱን እንዲሰጡ ብቃታቸው በሶስተኛ ወገን ያልተረጋገጠ መሆናቸው፤

2.2 <u>በጤና ዘርፍ</u>

የጤና ባለሙያዎች ማለትም የሕክምና ዶክተሮች፤ የጤና መኮንኖች፤ ነርሶች፤ የፋርማሲ ባለሙያዎችና፤ የሕክምና መሣሪያ ባለሙያዎች የምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት የሚያገኙት ከምግብ መድሐኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ባለሥልጣን ነው።

የኢትየጵያ የጤና ባለሙያዎች ምክር ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 76/2002 የተቋቋመና በጤናው ዘርፍ የምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄዎችን መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ባለሥልጣኑን የሚያግዝ ከሙያው ጋር ቅርበት ያለው አካል ነው።

ለጤና ባለሙያነት ምዝገባ የሚያስፈልገው የትምህርትና፤ የኢንተርንሺፕና የሥራ ልምድ ማስረጃ ሲሆን የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግለው ለአምስት ዓመት ብቻ ነው። ለእድሳትም ተመሣሣይ መስፈርት ያገለግላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የተከታታይ የሙያ ማበልፀጊያ መርሐ ግብር ለመጀመር ዝግጅት ተደርጎ እንደነበር ይታወቃል። ሲጠቃለል፤ በጤናው ዘርፍም ጥንካሬ ባይኖረውም ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና አለ፤ ተከታታይ የሙያ ልማትም በተለይም ለሕክምና ዶክተሮች ለመተግበር ጥረት እየተደረገ እንደነበር ሆኖም ውጤት ላይ ያልተደረሰ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያሳያል።

በሌላ በኩል በተለያዩ የጤና ተቋማት ውስጥ የተሳሳተ መድሐኒት ከመስጠት ጀምሮ፤ ለዘላቂ ጉዳት ወይም ለሕልፈተ ሕይወት የሚዳርግ ሥራ በሕክምና ስም እንደሚሠራ በመገናኛ ብዙሃን አልፎ አልፎ የሚሰሙ ዜናዎች እየሆነ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም፤ በጣም ጥቂት ባለሙያዎች ተጠያቂ እንደሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን ጥብቅ ክትትል ስለማይደረግ በዜጎች ላይ ከሚደርሰው የሕይወትና የአካል ጉዳት አኳያ ብዙም የሚያረካ ሥራ አልተሠራም።

2.3 <u>በአገር ውስጥ ልምድ የሚታይ ክፍተት</u>

ልምድ ከተወሰደባቸው አገሮች መታየትና እንደተሞክሮ መውሰድ ያለባቸው ብዙ ነጥቦች አሉ። ምንም እንኳ በሙያ ብቃት ማረጋጫ አካሄድ ላይ ልዩነቶች ቢኖሩም ካሉት ሂደቶች ውስጥ የጋራ የሆኑትን አውጥቶ ወደ አገራዊ ሁኔታ መውሰድ ይቻላል። በአብዛኛዎቹ አገራት የሚያመሳስላቸው፣

ሀ) በአገር ደረጃ የባለሙያዎች አንድ ወጥ የብቃት ማረጋገጫ የሚያከናውን ህጋዊ ሰውነት ያለውና የብቃት ማረጋገጫውን አገልግሎት ለመስጠት እውቅና የተሰጠው እንዳለ፤

ለ) ከብቃት አረጋጋጭ ጋር የሙያ ማህበራት በሙያ ማረጋገጫ ሂደት ላይ እና ቀጣይነት ያለው የሙያ ማሻሻያ ሂደቶች ላይ በጋራ የሚሰሩ መሆናቸው፤

ሐ) የባለሙያዎችን ብቃት ግምገማ የሚመሰረተው በትምህርትና በሥራ ልምድ ላይ የተመሠረተ ሣይሆን፤ ስልጠናና ፈተና የሚያካትት መሆኑ፤

መ) ተጨባጭ የሙያ ብቃት ልዩነት የሚጠይቁ በብዛታቸው ግን አነስተኛ የባነ የባለሙያ ደረጃዎች የሚያካትቱ መሆኑ፤

ሠ) የተለያዩ ባለሙያዎች አገልግሎቱን ለማግኘት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን በብዛታቸው ግን አነስተኛ የባነ የባለሙያ ደረጃዎች የሚያካትቱ መሆኑ፤

በሌላ በኩል ቀደም ብሌ እንደተጠቀሰው፤ የባለሙያ ምዘገባና ብቃት ማረጋገጫን በተመለከተ ያለውን ክፍተት ለመለየት አጥኒ ቡድኑ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች፤

1) ከመረጃ መረብ የሌሎች አገሮች ሥርዓቶች የተቋቋሙበትንና ያላቸውን ልምድ ማጥናት፤

2) የአገር ውስጥ ሥርዓቶች የተቋቋሙበትንና አሁን የሚገኙበትን ደረጃ መገምገም፤

3) ከባለድርሻ አካላት መረጃ በአውደ ጥናት፤ በቡድን ውይይትና በመጠይቅ ማከፋፈል መሰብሰብና የተገኘውን መረጃ ከሌሎች አጋራት ልምድ ጋር ማወዳደር ናቸው።

2.3.1 <u>በምክክር ስብሰባ የተገኘ ኃሳብ</u>

የሙያ ማህበራት ተወካዮች እና የተመረጡ የሴክተር ሚኒስቴር ተወካዮች በተገኙበት የምክክር ስብሰባ እ.ኤ.አ መጋቢት 24/2017 በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ስብሰባ አዳራሽ ተካሂዷል። የስብሰባው አላማም በአሁኑ ወቅት ያለው የምዝገባ ብቃት ማረጋገጫ ስርአት ላይ ያሉት ችግሮች ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን እይታ ለመዘገብ ሲሆን፤ በተሳታፊዎች ከተነሱት ችግሮች መካከል በከፊል የሲስተም ችግሮች፤ በከፊል ደግሞ የመስሪያ ቤቶቹና የድርጅቶች ችግሮች ናቸው።

ምንም እንኳን በርካታ ችግሮች ቢነሱም በሙያ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ጠቃሚ የሆኑ ዋና ዋና ነጥቦች በሚከተለው መልኩ ተጠቃለው ቀርበዋል።

1. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ብቻ ሳይሆን በሙያ ምዝገባና ማረጋገጫ ስርአት ላይም ችግር መኖሩ፤
2. ያልተሸፈኑ ዘርፎች እና የተለያዩ የሙያ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ስርአት ኃላፊነቶች ተደራርበው መኖር፤

3. የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጡ ተቋማት እውቅና የሚሰጡበትና የሚያገኙበት ተገቢው ስርአት አለመኖር፤
4. በወቅቱ ባለው የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ ስርአት ውስጥ የሙያ ማህበራትና የትምህርት ተቋማት ተሳትፎ አለመኖር የሚሉት ናቸው።

3 በባለሙያ ብቃት ምዘናና ምዝገባ የተመረጡ የውጭ አገራት ልምድ

3.1 በምህንድስና ዘርፍ

በርካታ አገራት የባለሙያ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ሰፊ ልምድ እንዳላቸው ይታወቃል። ሆኖም ያላቸው ልምድ በአብዛኛው ተመሣሣይ በመሆኑ ሁሉንም አገራት መዳሰሱ አስፈላጊ ባለመሆኑ፤ በቂ ትምህርት ሊገኝባቸው ይችላል ተብሎ የሚታመንባቸውን የአሜሪካን፤ የካናዳንና የእንግሊዝን ልምዶች በአጭሩ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል።

የአሜሪካን ልምድ

የምህንድስና ምዝገባ በየክፍለ መንግሥታቱ የተቋቋሙና ብሔራዊ የፈተና ምክር ቤቶችን ያካተቱ ሕጋዊ የምህንድስና ምዝገባ ቦርዶች ሲሆን፤ አብዛኛዎቹ ቦርዶች ለባለሙያ ምዘገባ የሚከተሉት አራት ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ይጠብቃሉ፤

1) ከታወቀ የምህንድስና መርሐ ግብር የተመረቀ/ች
2) የመጀመሪያውን መሠረታዊ ምህንድስና ፈተና ከመመረቁ በፊት ወይም ከተመረቀ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ተፈትኖ ያለፈ/ችና በተለማማጅ መሐንዲስነት የተመዘገበ፤
3) በአማካይ የአምስት ዓመት የተግባር ልምድ ያገኘ/ች
4) የሁለተኛውን የምህንድስና መርሐችና ተግባራት ፈተና በአጥጋቢ ውጤት ያለፈ/ች

እነዚህ አራት መስፈርቶች ከተሟሉ፤ ባለሙያ መሐንዲስ (Professional Engineer) የሚል ስያሜ ያሰጣሉ። በምህንድስና ሥራዎች ላይም ይሳተፋሉ። የሙያ ስህተት ለሚፈፅሙ ባለሙያዎችም እንደ ስህተቱ ዓይነት ምዝገባቸው ለተወሰነ ጊዜ የሚታገድ ወይም የሚሰረዝ እንደሆነ በሕጉ የተቀመጠ ጉዳይ ነው።

የካናዳ ልምድ

በሕጉ መሠረት የባለሙያ መሐንዲስ በሚል ስያሜ ሊጠቀሙ የሚችሉት ፍቃድ ያላቸው መሐንዲሶች ብቻ ነው። ይህንንም ስያሜ የሚሰጡት ተግባሩን እንዲያከናውኑ የማህበረ ሰቡን ደህንነትና ጤንነት እንዲጠብቁ ኃላፊነት በዓዋጅ የተሰጣቸው እንደግል ተቋማት የሚንቀሳቀሱ የሙያ ማህበራት ናቸው።

1) በካናዳው የምህንድስና ዕውቅና ቦርድ ከታወቀ የምህንድስና ወይም አፕላይድ ሳይንስ መርሐ ግብር የተመረቀ/ች

2) በተመዘገበ ባለሙያ መሐንዲስ ሥር በተለማማጅ መሐንዲስነት ቢያንስ አራት ዓመት (በኪውቤክ ለየት ይላል) የሠራ/ች፤

3) የተመዘገበው የተግባር ልምድ በሙያ ማህበር የተፈተሸለት/ላት፤

4) የምህንድስና ተግባር ፈተና በአጥጋቢ ውጤት ያለፈ/ች

የምህንድስና ሥነ ምግባር ኮድ መጣስ፤ የሙያ ፍቃድ ከመነጠቅ ጀምሮ በተለይም የሕይወት መጥፋት በተከሰተበት ሁኔታ ለእሥር የሚዳርግ ቅጣት የሚጣልበት እንደሆነ በግልፅ ይታወቃል።

<u>የእንግሊዝ ልምድ</u>

የእንግሊዙ የምህንድስና ምክር ቤት የቻርተርድ እና የኢንኮርፖሬትድ ኢጀነርስ ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ሥልጣን የተሰጠው ሕጋዊ አካል ነው። ማንኛውም ባለሙያ ምዝገባ እንዲኖረው ከ 8-12 ዓመት የሚደርስ የከፍተኛ ትምህርት መርሐ ግብር ማጠናቀቅና በቀደምት ባለሙያ ሥር ተገቢውን ክህሎት የሚያስጨብጥ ሙያዊ ልምምድ ማድረግ ይጠበቅበታል።

የሶስት ዋና ዋና አገራት ልምዶች የቀረቡት በቂና መሠረታዊ ኃሣብ ለማስጨበጥ ያስችላሉ በሚል እምነት ቢሆንም አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ የአገራት ልምዶችን ማካተት ይቻላል። ይሁን እንጂ ምንም ተጨማሪ ግንዛቤ የማይሰጥ በመሆኑ አልተካተተም።

3.2 <u>በጤና ዘርፍ</u>

በሠለጠኑት አገራት በአሜሪካም ሆነ በካናዳ ወይም በአውሮፓ ከምህንድስና ዘርፍ በጠነከረ መልኩ በጤና ዘርፍ ቁጥጥር እንደሚደረግና፤ በአብዛኛው የጤና ባለሙያዎች አገልግሎት ለመስጠት በሙያ ምዝገባና ምዘና ሥርዓት ውስጥ እንዲቆዩ የሚያስገድዷቸው የሕግ ማዕቀፎች እንዳሉ ይታወቃል። አብዮቹም ሥርዓቶች ተመሣሣይ በመሆናቸው እንደምሣሌ ለመጠቀም ሶስት የተለያዩ ሥርዓቶች መጥቀስ በቂ ግንዛቤ ይሰጣል። ይህም በአሜሪካን፤ በጀርመንና በአየር ላንድ ሪፑብሊክ ውስጥ በሥራ ላይ ያለውን የጤና ሙያ ምዝገባና ምዘና ሥርዓት ነው።

በአሜሪካን አገር እያንዳንዱ ግዛት (State) የራሱ የሆነ የምህንድስናም ሆነ የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና ምዘና ደንብ ቢኖረውም ልዩነቶቹ ትንሽ በመሆናቸው አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘት በቂ ነው።

በሁሉም የአሜሪካን ግዛቶች የሐኪምነት ብቃት ማረጋገጫና ፍቃድ ማግኘት ግድ ይላል። ለዚህም ከታወቀ ዩኒቨርስቲ መመረቅ፤ በተመረጡ የጤና ተቋማት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት መስጠት፤ እንዲሁም አራት የእውቀትና የተግባር ክህሎት መለኪያ

ፈተናዎችን በተለያየ ጊዜ መፈተን ያስፈልጋል። በግዛቶቹ ውስጥ ያለው ልዩነት የአገልግሎት ጊዜ፤ በየፈተናዎቹ መሐል የሚያስፈልገው ጊዜና ሌሎች ጥቃቅን አሠራሮች ናቸው።

በሌላ በኩል፤ በጀርመን አገር በሥራ ላይ ያለው ብቃት ማረጋገጫና ፍቃድ አሰጣጥ ሥርዓት በሶስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ከምረቃ ሁለት ዓመት በኋላ በሚወስደው ፈተና ሲሆን ሁለተኛው ምዕራፍ ከሶስት ተጨማሪ ዓመታት በኋላና ሶስተኛው ምዕራፍ የሚጀምረው ከአንድ ተጨማሪ ዓመት በኋላ በሚሰጥ ተግባር ተኮር ፈተና ነው። ሁሉንም ፈተና ማለፍ የጤና ሙያ ብቃት ማረጋገጫና ፍቃድ ለማግኘት ወሳኝ ነው።

በአየርላንድ የሕግ ማዕቀፉ ሜዲካል ፕራክቲሽነርስ አክት (Medical Practitioners Act) በመባል ይታወቃል። በማዕቀፉም የጤና ሙያ ምዝገባና ምዘና እንዲያካሂድ ሥልጣን የተሰጠው ሜዲካል ካውንስል (Medical Council) ባለሙያዎች ከታወቀ የትምህርት ተቋም መመረቅ እንዳለባቸው፤ በየዓመቱ በተወሰነ ተከታታይ የሙያ ማበልፀጊያ ተግባር ውስጥ ለተሳተፉ ብቻ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንደሚሰጥ፤ ይህንንም ማረጋገጫ ያልያዘ ባለሙያ አገልግሎት መስጠት እንደማይችል በግልፅ ተጠቅሷል።

የሙያ ማበልፀጊያ መስፈርት በተለያየ መንገድ ለምሳሌ በአጭር ጊዜ ስልጠና፤ በሙያዊ ስብሰባ ወይም ውይይት፤ ወይም ሙያዊ ልምዶ ሊሟላ ይችላል። በመመሪያውም መሠረት እነዚህ የተለያዩ ሙያዊ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ ክሬዲቶች በመመዝገብ የሙያ ምዘና መስፈርቱ የሚጠይቀውን አጠቃላይ ውጤት እንዲያሟሉ ይጠበቃል።

4 <u>አዲሱ የባለሙያዎች ብቃት ምዘናና ምዝገባ አዋጅ ፋይዳ</u>

በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የባለሙያዎች ብቃት ምዘናና ምዝገባ ስርዓት አስፈላጊ ከሆነበት ምክንያት መካከል፡-

በአገራችን እየተካሄደ ካለው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ጋር የተጣጣመ የባለሙያዎች ብቃት ለማሳደግ፤ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጥራትና ሥነ ምግባር የተሞላበት የሙያ አገልግሎት መስጠት እጅግ አስፈላጊ እየሆነ የመጣ በመሆኑ፤ በተለይም በምህንድስናና በጤና ዘርፎች ውስጥ የሚታዩት የጥንቃቄ ጉድለቶች በማህበረሰብ ውስጥ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑና እነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የተጠናከረ የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፤

ይህ አዋጅ ዋነኛ ዓላማ ያደረገው፡-

- በተለያዩ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ተበታትኖ የሚሰጠውን የባለሙያ ምዝገባና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓቶች አንድ ወጥ በሆነና በተሟላ መልኩ መስጠት፤
- በተለያዩ ዘርፎች ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን እውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት መያዛቸውን በትክክል ማረጋገጥና የሙያ ብቃት ምዘናና ምዝገባ አገልግሎት መስጠት፤
- የባለሙያዎችን ብቃት በመቆጣጠር ከሙያ ብቃት ማነስና ስነምግባር ጉድለት ጋር ተያይዞ በህዝብ ደህንነት እና ጤንነት ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችን መከላከል ነው።

4.1 ብሔራዊ የባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ብቃት ምዘና ባለስልጣን ተልእኮ

አዋጁ ከላይ የጠቀሳቸውን ዓላማዎች ለማሳካት ብሔራዊ የባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘናና ምዝገባ ባለስልጣን መቋቋም እንዳለበት ረቂቅ ሃሳብ ቀርቧል

ይህ ተቋም ተልእኮውን ለማሳካት ከልዩ ልዩ የሙያ ማህበራት፤ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር አብሮ እንሚሰራ ተደንግጓል። ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት ከብልሹ አሰራር የጸዳ እንዲሆን የሙያ ብቃት ምዘና አሰራሩ ከሙያ ማህበራት በተውጣጡ ባለሙያዎች እንዲከናወን ተደርጓል። ቅሬታዎች ካሉም ከልዩ ልዩ ሙያ ማህበራት ሰብሳቢዎች በተውጣጣ ኮሚቴ እንዲታይ ተደርጎ ተቀርፃል። የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ቢሆን ከተለያዩ ሚ/ር መስሪያቤቶች በኩል የሚቀርቡ የጥቅም ግጭትን ያስወግዳል የሚል ሃሳብ ቀርቧል። ተቋሙ የሙያ ብቃት ምዘና በማካሄድ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከመስጠትና ማደስ በተጨማሪ ለባለሙያዎች የሙያ ማበልፀጊያ ዕድሎችን የማመቻቸትና የማከናወን ኃላፊነትም ተሰጥቶታል፤

የሚቋቋመው ባለስልጣን መስሪያቤት የባለሙያዎች ብቃት መመዘንና ምዝገባ ለማካሄድ የሚያስችለውን ቁመና በመያዝ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት እውቅና እንዲያገኝ ሚደረግ ሲሆን ይህ እውቅና ባለስልጣን መስሪያቤቱ በተዋረድ ለባለሙያዎች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሃገራችን ባለሙያዎች በሌሎች ሀገራት ሄደው በሙያቸው መስራት የሚያስችላቸውን እውቅና የሚያስገኝ በመሆኑ የባለሙያዎቻችንን የረዥም ጊዜ ጥያቄ የሚመልስ ነው።

የባለሙያዎችን የሙያ ስነምግባርን መከታተልና ሙያ ስነምግባር ጥሰት ተጥሰው ሲገኙ እንደ ጥፋቱ ክብደት ባለሙያውን ከማስጠንቀቅ ጀምሮ እስከ ማገድ ወይም ምዝገባውን እስከመሠረዝ የሚደርስ ቅጣት የመጣል ስልጣን ለተቋሙ ተሰቷል። በተጨማሪም ስነምግባር ጉድለት ያለባቸው ሙያተኞች በወንጀል የሚያስቀጡ ጥፋቶችን ፈጽመው ሲገኙ ከሚመለከታቸው የፍትህ አካለት ጋር በመቀናጀት ህግን የማስፈጸም ተልእኮ ኖረዋል። ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ስራዎች በበላይነት የሚቆጣጠርና ስትራቴጂክ አቅጣጫወችን የሚሰጥ ቦርድ በበላይነት እንዲመራ ተደርጎ ተቀርፃል።

5 ማጠቃለያ

የባለሙያ ምዝገባና ሙያ ብቃት ማረጋገጥ ለአገራችን እንግዳ አይደለም። ከአምስት በላይ የዘርፍ መሥራያ ቤቶች አገልግሎቱን እንደሚሰጡ ይታወቃለ። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሌላ ተጨማሪ መሥሪያ ቤት ለማቋቋም ሳይሆን፤ እስካሁን ድረስ ይሰጡ የነበሩትን የባለሙያ ምዝገባና ሙያ ብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች የሚተካ አዲስ ብሔራዊ ወጥ የአንድ መስኮት አገልግሎት በሥራ ላይ ማዋል ነው።

የመጀመሪያው ጥያቄ ለምን አዲስ ሥርዓት አስፈለገ? ወይም አዲሱ ሥርዓት አሁን በሥራ ላይ ያሉት ሥርዓቶች የታየባቸው ችግር እንደማይገኝበት ምን ማረጋገጫ አለ? የሚል ነው።

አንዱ መልስ በአሁኑ ወቅት ተበታተነው የሚገኙት አገልግሎቶች በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የሙያ ግድፈትና በዚህም እየጨመረ የመጣውን የማህበረ ሰብ ደህንነትና ጤንነት አደጋ ሊቆጣጠሩ ባለመቻላቸውና ይህም የሆነበት ምክንያት የሙያ ብቃት ማረጋገጥ ሥራው አግባብ ባለው ቢሮ ዕውቅና ስለሌለውና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ባለመኖሩ ነው።

ሌላው አገልግሎቱ ተከታታይ የሙያ ማበልፀግን ስለማያካትትና ምዘናው በደጋፊ ሰነዶች ምርመራ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ባለሙያዎች ሙያቸውን ለማዳበር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ስለማያደርጉ ነው። ይህ ችግር ሁሉም ሙያዎች ላይ የሚታይ ቢሆንም፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በዘርፉ ከሚካተቱት ዋና ዋና ሙያዎች ውስጥ ለምህንድስናና የጤና ሙያዎች ትኩረት ቢሰጥ ለማህበረሰቡ ደህንነትና ጤንነት ጉልህ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው በማመን ይህን ረቂቅ አዋጅ እንዲዘጋጅ ወሰኗል።

ጥናቱ በአገር ውስጥ በውጭ አገር ልምዶች ላይ ተመሥርቶ፤ በምክክር ስብሰባዎች ውይይቶች ዳብሮ የቀረበ ሲሆን፤ የጥናቱ መሠረታዊ ውጤት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሥር የሚዋቀር የባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ቢቋቋም በሁለቱ የሙያ ዘርፎች የሚታየውን ችግር ሊያቃልል ይችላል የሚል ነው። የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከሙያ ማህበራትና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በቅርብ የሚሠራ ሲሆን በ 2011 ጀምሮ ወደ ሥራ በመግባት ለሙያ እድገት ለባለሙያ ጥንካሬ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያደርግ እንደሚችል የታመነ በመሆኑ መንግስት የቀረበውን ረቂቅ ሰነድ በመመርመርና በማዳበር ስራ ላይ እንደሚውል በመተማመን ነው።